


# የጀርመንኛ ኮርስና ፈተና

## ጥር 2018 እስከ ጥር 2019

በጎተ ኢኒስቲቱት ኢትዮጵያ

GOETHE INSTITUT

Sprache. Kultur. Deutschland.






# መደበኛ ኮርሶች

## ከ16 አመት በላይ ለሆኑ ተሳታፊዎች

ጀርመንኛ ከባለሙያዎቹ ዘንድ ይማሩ፤ የጎተ ኢኒስቲቱት አዲስ አበባ ኤክስቴሲቭ ፣ ኢንቴንሲቭና ሱፐር ኢንቴንሲቭ ኮርሶችን አሰናድቶ ይጠብቆታል። የደረጃ መለኪያ ፈተና በመውሰድ በውጤቱ መሠረት የሚገባዎት ኮርስ ውስጥ ይመደባሉ። የጀር መንኛ ቅድሚያ እውቀት ከሌለዎ ከ ኤ 1 የመጀመሪያ ደረጃ ይጀምራሉ። ኮርሶቻችን ጠዋት፣ከሰዓት በውኋላና ማታ ይሰጣሉ።

### ኤክስቴንሲቭ ኮርሶች (ኤ 1.1 - ሲ1.2)

· ኮርሱ የሚቆይበት ጊዜ፥ 7 ሳምንታት (ኤ 1.1- ሲ1.2)
· የሚጀምርበት ወራት፥  ጥር፣መጋቢት፣ግንቦት፣ሐምሌ፣መስከረም፣ህዳር
· በሳምንት፥ 3  ጊዜ (በአንድ ቀን 3 የትምህርት ክፍለ ጊዜ)
· ለኤ1.1-ሲ1.2  72 የትምህርት ክፍለ ጊዜ
· የተሳታፊ ቁጥር፥ ቢያንስ 12 ቢበዛ 18

#### የኮርስ ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

### ኢንቴንሲቭ ኮርሶች ( ኤ 1.1 እስከ ቢ1.2)

· ኮርሱ የሚቆይበት ጊዜ፥  7 ሳምንታት
· የሚጀምርበት ወራት፥ ጥር፣መጋቢት፣ግንቦት፣ሐምሌ፣መስከረም፣ህዳር
· በሳምንት፥ 4  ጊዜ (በአንድ ቀን 3 የትምህርት ክፍለ ጊዜ)
· በአጠቃላይ 84 የትምህርት ክፍለ ጊዜ
· የተሳታፊ ቁጥር፥ ቢያንስ 12 ቢበዛ 18

#### የኮርስ ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

## ሱፐር ኢንቴንሲቭ ኮርሶች ((ኤ 1፣ ኤ2፣ ቢ1)

በፍጥነት (ሰባት ሳምንታት) አንድ ሙሉ ደረጃ ለማጠናቀቅ ለሚፈልጉ

· ኮርሱ የሚቆይበት ጊዜ፥ 6 ሳምንታት
· የሚጀምርበት ወራት፥ ጥር፣መጋቢት፣ግንቦት፣ሐምሌ፣መስከረም፣ህዳር
· በሳምንት፥ 5 ጊዜ (በአንድ ቀን 5 የትምህርት ክፍለ ጊዜ)
· በአጠቃላይ 147 የትምህርት ክፍለ ጊዜ
  ከ3 የትምህርት ክፍለ ጊዜ የፈተና ዝግጅት ጋር
· የተሳታፊ ቁጥር፥ በትንሹ 10 ቢበዛ 15

### የኮርስ ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

## በጋብቻ ምክንያት ለሚማሩ የተዘጋጀ ኮርስ (ኤ1.1 ፤ ኤ1.2)

ይህ ኮርስ ከትምህርት ለረጅም ጊዜ ለራቁና የጋብቻ አጋራቸው በጀርመን ሀገር ሆኖ ከጋብቻ አጋራቸው ጋር ለመቀላቀል ለሚፈልጉ የተሰናዳ ነው።

· ኮርሱ የሚቆይበት ጊዜ፥ 7 ሳምንታት
· የሚጀምርበት ወራት፥ ጥር፣መጋቢት፣ግንቦት፣ሐምሌ፣መስከረም፣ህዳር
· በሳምንት፥ 5 ጊዜ (በአንድ ቀን 3 የትምህርት ክፍለ ጊዜ)
· በአጠቃላይ 105 የትምህርት ክፍለ ጊዜ
· የተሳታፊ ቁጥር፥ ቢያንስ 12 ቢበዛ 18

### የኮርስ ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

## የታዳጊዎች ኮርስ

ለታዳጊዎች (ከ 11 እስከ 15 ዓመት)

· ኮርሱ የሚቆይበት ጊዜ፥ 16 ሳምንታት
· የሚጀምርበት ወራት፥ መጋቢት፣መስከረም
· በሳምንት፥ 1 ጊዜ (በአንድ ቀን 4 የትምህርት ክፍለ ጊዜ)
· በአጠቃላይ 64 የትምህርት ክፍል ጊዜ
· የተሳታፊ ቁጥር፥ ቢያንስ 12 ቢበዛ 18

### የኮርስ ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

## ኦላይን ኮርስና ቅይጥ ኮርስ

ኦልይን ኮርስ ሙሉ በሙሉ በኢንተርኔት የሚሰጥ ሲሆን በሳምንት አንድ ባጠቃላይ 8 በኢንተርኔት የቀጥታ ክፍል ይኖረዋል።
ቅይጥ ኮርስ የምንለው በሳምንት ሁለት ጊዜ በዙም ቀጥታ የሚሰጥብትና በቀረው ጊዜ በኦን ላይን የሚሰራ ትምህርት ነው።

· ኮርሱ የሚቆይበት ጊዜ፥ ሰባት ሳምንት
· የሚጀምርበት ወራት፥ ጥር፣መጋቢት፣ግንቦት፣ሐምሌ፣መስከረም፣ህዳር
· በአጠቃላይ 63 የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለኦንላይን ኮርስ፣
· 72 የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለቅይጥ ኮርስ (35 ክፍለ ጊዜ በዙም ቀጥታ)
· የተሳትፊ ቁጥር፥ በትንሹ 12 ቢበዛ 18

### የኮርስ ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

## የፈተና ዝግጅት ኮርሶች

በነኝህ የፈተና ዝግጀት ክፍሎች ለስታርት ዶች 1 (ኤ 1)፣ ለጎተ ሰርተፊኬት ቢ 1 ይዘጋጃሉ። የፈተናዎቹን የጽሑፍ እና የቃል ክፍሎቹን እናስተዋውቆታለን። የተለያዩ የፈተና መለማመጃዎችን በማሰራት፣የጊዜ አጠቃቀሞትን በማሻሻልና የናሙና ፈተና ዎችን በማሳየት ለፈተናው እናዘጋጅዎታለን።

· ኮርሱ የሚቆይበት ጊዜ፥ 4 ሳምንታት
· የሚጀምርበት ወራት፥ ጥር፣ መጋቢት፣ ግንቦት፣ ነሐሴ፣ ጥቅምት፣ህዳር
· በሳምንት ሁለት ጊዜ (በአንድ ቀን 4 የትምህርት ክፍለ ጊዜ)
· በአጠቃላይ 32 የትምህርት ክፍል ጊዜ (አንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ፡- 45 ደቂቃ)
· ተሳታፊ ቁጥር፥ በትንሹ 12 ቢበዛ 18

### የኮርስ ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

የጎተ ኢኒስቲቱት በሁሉም የቋንቋ ደረጃ የተዘረዘሩት ኮርስች በታቀደላቸው ቀጠሮዎች መሠረት እደሚሰጡ ዋስትና መስጠት አይችልም።



# የኮርስ ምዝገባ

| የኮርስ ምዝገባ ቀናት | የኮርስ ጊዜ |
|---|---|
| ታኅሣሥ 24 እስከ ጥር 9 | ጥር 12 እስከ የካቲት 27 |
| የካቲት 30 እስከ መጋቢት 10 | መጋቢት 14 እስከ ሚያዚያ 30 |
| ግንቦት 3 እስከ ግንቦት 14 | ግንቦት17 እስከ ሐምሌ 3 |
| ሀምሌ 6 እስከ ሐምሌ 17 | ሐምሌ 20 እስከ መስከረም 01 |
| መስከረም 4 እስከ መስከረም 15(2019) | መስከረም 18 እስከ ጥቅምት 27 (2019) |
| ጥቅምት 30 እስከ ኅዳር 11 | ኅዳር 14 እስከ ታኅሣሥ 22 |
| ታኅሣሥ 26 እስከ ጥር 7 | ጥር 10 እስከ የካቲት 26 |

| | |
|---|---|
| የምዝገባ ክፍያ | 50 ብር |

የምዝገባ ቀናት ሊቀየሩ ስለሚችሉ ድረ-ገጻችንን **www.goethe.de/addisabeba** ይጎብኙ።

## የምዝገባና የተሳትፎ ደንቦች

ማንኛውም የኮርስ ወይንም የፈተና ክፍያ ሙሉና በጥሬ ብር ይደረጋል። ለቋንቋ ትምህርት የተከፈለ ክፍያን መመለስ የሚቻለው:-

የታቀደው ትምህርት ሊሰጥ የማይችል ሲሆን፣ ተመዝጋቢው/ዋ በትምህርቱ ላይ መሳተፍ ሳይችል/ሳትችል ሲቀርና ይህን ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት አሳውቆ/አሳውቃ የከፈለው/ችው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግለት/እንዲደረግላት ሲጠይቀ/ስትጠይቅና የኮርስና የመጽሐፍ ደረሰኝ ይዞ/ዛ ሲቀርብ/ስትቀርብ ብቻ ነው። የምዝገባ ክፍያ አይመለስም። ለኮርሱ የተገዛ መጽሐፍ ለተቋሙ ይመለሳል። የኮርስ ክፍያም ሆነ የኮርስ ተሳትፎ ከተከፈለበት ጊዜ ውጭ  ለሌላ የኮርስ ጊዜ ወይንም ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይቻልም። የመማሪያ ሰዓት መቀየር የሚቻለው የቋንቋ ቢሮ ሲፈቅድ ብቻ ነው። የፈተና ክፍያ የሚመለሰው ተፈታኙ ፈተናውን መፈተን የማይችልበትን ጉዳይ ከፈተና ቀን በፊት በማስረጃ አስደግፎ ሲያቀርብ እና በፈተና ኃላፊው ምክንያቱ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ ተቋሙ ሃያ በመቶ የምዝገባ ወጭ ቀንሶ ቀሪውን ይመልስለታል።

ኮርሱ ሊሰረዝ የሚችለው ፥ በቂ ተማሪዎች ሳይኖሩ፣ አስተማሪ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ማስተማር እንደማይችል ሲያስታውቀንና ከተቋማችን አቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ተቋማችን ኮርሶችን ከመጀመራቸው በፊት ሊሰረዝ ይችላል።

የኮርስ ተሳታፊዎች ለምዝገባ ሲመጡ አንድ ፎቶ የኢሜል አድራሻና  መታወቂያ ይዘው መቅረብ አለባቸው። ከጠቅላላው የትምህርት ክፍል ጊዜ ሰባ በመቶ እና ከዚህ በላይ የተሳተፈ እና አራት የክፍል ፈተናዎችን የተፈተነ ለኮርሱ ሰርተፊኬት ይሰጠዋል። ሰርተፊኬቱን ልንሰጥ የምንችለው ተከታዩ ኮርስ በሚጀምርበት ሳምንት ነው።

ኮርሱ ከመጠናቀቁ በፊትም ሆነ በኋላ የሚጠየቅ ማንኛውም አይነት ተጨማሪ ማረጋገጫ በአንድ ማረጋገጫ 50 ብር ያስከፍላል፡፡ የደረጃ መመደቢያ ፈተና 200 ብር ያስከፍላል።ትምህርቱ የሚሰጠው የላቲን ፊደላትን በመጠቀም ነው፡፡ የላቲን ፊደል ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ግለሰቦችን የመርዳት አቅም ስለሌለን ከውጭ ይህን ቅደመ-ሁኔታ አሟልተው እኛ ዘንድ ለቋንቋ ትምህርት እንዲመጡ እናሳስባለን።

የኮርስ ተሳታፊዎች የተቋሙን ደንብ ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

# በአውሮፓ የጋራ የቋንቋ ችሎታ መመዘኛ መደብ መሠረት የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ ደረጃዎች

የመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋ አጠቃቀም

## A1 (A1.1 / A1.2)

እለት በእለት የሚደረጉ የተለመዱ ንግግሮችንና ሀረጎችን ይረዳል እንዲሁም ይጠቀምባቸዋል። እራሱን ሊያስተዋውቅና ሌሎችን ስለራሳቸው (ለምሳሌ የት እንደሚኖሩ፣ ማንን እንደሚያውቁ ወይም ምን እንዳላቸው) ሊጠይቅ ይችላል። አብረውት ያሉት ተናጋሪዎች በዝግታና በግልፅ እንዲሁም ለመርዳት ዝግጁ ሆነው ከተናገሩ ሊግባባና ሊረዳ ይችላል።

## A2 (A2.1 / A2.2)

አረፍተ ነገሮችንና በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ንግግሮችን (ለምሳሌ የግልና የቤተሰብ መረጃ ፣ገበያ መገበያየት፣ ስለስራ፣ በቅርብ ስላለ መኖሪያና አካባቢ) ይረዳል። በቀላልና በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ በሚውሉ ንግግሮች መግባባት ይችላል እንዲሁም በቀላል አረፍተ ነገሮች ከየት እንደመጣ ፣ስለትምህርት ሁኔታው በአስፈላጊው ቦታ ላይ መጠቀም ይችላል።

እራስን ችሎ በቋንቋ የመጠቀም ደረጃ

## B1 (B1.1 / B1.2)

በስራ ቦታ ትምህርት ቤት ፣ስለ እረፍት ጊዜ ወ.ዘ.ተ የሚነገረውን ደረጃውን የጠበቀ ቋንቋ መሰረታዊ ሂደት ይረዳል። በአብዛኛው በጉዞ ላይ ሊያጋጥም የሚችለውን የቋንቋ አጠቃቀም መወጣት ይችላል። ስለሚያውቀው ርእስ በቀላሉና በተያያዘ ሁኔታ ፣ስለ ግል ፍላጎቱ፣ስለ ልምዱ ፣ስለተፈጠሩ ሁኔታዎች ፣ስለወደፊት ምኞቱ ፣ስለ ተስፋውና ሊደርስበት የሚፈልገውን ግብ፣እቅዱን፣አስተያየቱን በአጭሩ መግለጽና ማስረዳት ይችላል።

## B2 (B2.1 / B2.2)

ቀጥተኛና በቀላሉ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ርእሶችን የያዙ ፅሁፎችን ይዘት እንዲሁም በተማረው የትምህርት ዐይነት የሚደረጉ ውይይቶች መረዳት ይችላል። ጀርመንኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከሆኑ ሰዎች ጋር በፍጥነትና ያለምንም ችግር መግባባት ይችላል፡፡አንድን ሰፋ ያለ ርእስ በዝርዝር መግለፅ ይችላል። እንዲሁም በወቅቱ በተነሳ ጥያቄ ላይ ያለውን አቋም፣ ጠንካራና ደካማ ጎንን እንዲሁም አማራጮችን መስጠት ይችላል።

በማንኛውም ሁኔታ በቋንቋ የመጠቀም ችሎታ

## C1 (C1.1 / C1.2)

ሰፋ ያሉ ርእሶችንና ቀጥተኛ ያልሆኑ አባባሎችን መረዳት ይችላል።በፍጥነትና ያለምንም እንከን ቃላትን መፈለግ ሳያስፈልገው መናገር ይችላል። በማህበራዊ ኑሮና በስራ ላይ ወይም በትምህርት ላይ ቋንቋውን በብቃት ሊጠቀምበት ይችላል። የተወሳሰቡ ሁኔታዎችን መግለፅና በዚህም ላይ የተለያዩ የአንቀፅ ማያያዣዎችን መጠቀም ይችላል።

## C2 (C2.1 / C2.2)

ሁሉንም ይችላል፡፡ የሚያነበውንና የሚሰማውን ያለችግር መረዳት ይችላል። ከፅሁፍና ከቃል ምንጮች የሚገኙ መረጃዎችን አንድ ላይ ማቀነባበርና በተያያዘ ሁኔታ እንደገና ማቅረብ ይችላል። ምንም ሳይጨነቅ ያለዝግጅት በትክክል ውስብስብ ጉዳዮች ውስጥ የነገሮችን ግኑኝነት ግልፅ ማድረግ፣ ለዚህም ረቂቅ የቋንቋ ፈሊጦችን መጠቀም ይችላል።

# ፈተና

| ሰርተፊኬት | አስፈላጊነት |
|---|---|
| **Goethe-Zertifikat C2** | · ቋንቋውን ለማስተማር፣ለመተርጎም<br>· በጀርመን ዩኒቨርሲቲ ለመማር |
| **Goethe-Zertifikat C1** | · በአንዳንድ የጀርመን ዩኒቨርሲቶች ለመማር<br>· ለብዙ የሥራ መስኮች (ሕክምና ወዘተ) |
| **Goethe-Zertifikat B2** | · ወደሽቱዲን ኮሌግ ለመግባት<br>· በህክምና ዘርፍ ለመሥራት (ነርስ፣ሐኪም ወዘተ)<br>· በአስጎብኚነት ለመሥራት |
| **Goethe-Zertifikat B1** | · የጀርመን ዜግነት ለመውሰድ<br>· ጀርመን አገር የፍቃድኝነት አገልግሎት ዓመት ለማድረግ<br>· ጀርመን አገር የሙያ ትምህርት ቤት ለመግባት |
| **Goethe-Zertifikat A2** | · በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለሁለተኛ ዲግሪ ለመማር<br>· በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመጀመሪያ ዲግሪ ለመማር |
| **Goethe-Zertifikat A1 Start Deutsch 1** | · በሞግዚትነት በጀርመንና ኦስትሪያ ለመሥራት<br>· ወደጀርመንና ኦስትሪያ ለመሄድ<br>· ረጅም ጊዜ ጀርመን አገር ለመቆየት<br>· በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለሁለተኛ ዲግሪ ለመማር<br>· በእንግሊዝኛ ቋንቋ ልዩ ጥናት ለማድረግ (ሐኪም) |

የፈተና ቀናት በአጭር ጊዜ ሊቀየሩ ስለሚችሉ ከፈተናው ቢያንስ አንድ ሳምንት በፊት ድረ ገጻችንን **www.goethe.de/addisabeba** ይጎብኙ።



# የፈተና ምዝገባ

| ፈተና | ምዝገባ | የፈተና ቀናት |
|---|---|---|
| **Goethe-Zertifikat A1 Start Deutsch 1** | እስከ ታኅሣሥ 16<br>እስከ የካቲት 19<br>እስከ ሚያዚያ 15<br>እስከ ሰኔ 22<br>እስከ ነሐሴ 22<br>እስከ ጥቅምት 13<br>እስከ ታኅሣሥ10 | ጥር 4 - ጥር 6<br>መጋቢት 2 - መጋቢት 4<br>ግንቦት 10 - ግንቦት 12<br>ሐምሌ 8 - ሐምሌ 10<br>መስከረም 11 - መስከረም 13<br>ኅዳር 2 - ኅዳር 4<br>ጥር 5 - ጥር 7 |
| **Goethe-Zertifikat A1 Fit in Deutsch 1** | በጥያቄ | በስምምነት |
| **Goethe-Zertifikat A2 Fit in Deutsch** | በጥያቄ | በስምምነት |
| **Goethe-Zertifikat A2**<br>**Goethe-Zertifikat B1**<br>**Goethe-Zertifikat B2** | እስከ ጥር 22<br>እስከ  መጋቢት 17<br>እስከ ግንቦት 21<br>እስከ ሐምሌ 24<br>እስከ መስከረም 22 | የካቲት 9 እስከ የካቲት 12<br>ሚያዚያ 5 እስከ  ሚያዚያ 9<br>ሰኔ 8 እስከ ሰኔ 11<br>ነሐሴ 11 እስከ ነሐሴ 14<br>ጥቅምት 9 እስከ ጥቅምት 12 |
| **Goethe-Zertifikat C1** | በጥያቄ | በስምምነት |
| **Goethe-Zertifikat C2** | በጥያቄ | በስምምነት |

# የፈተና ክፍያ

ወቅታዊ የክፍያውን መጠን ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።
የውጭ ተፈታኞች በጎተ ኢኒስቱትት ለስድስት ወራት  በተከታታይ ኮርስ ያልወሰዱ ናቸው።

[1] የውጭ ተፈታኞች ለስድስት ወራት በተከታታይ ጎተ ኢኒስቲቱት ያልተማሩ ናቸው።

# ተጨማሪ አገልግሎት ለተማሪዎች

## መምህራን

ጎተ ኢኒስቲቱት የመምህራኑ የቋንቋ ብቃት ከፍትኛ ደረጃ ላይ መድረሱን እጅግ፣ ዘመናዊ በሆነው የቋንቋ ማስተማር ዘዴዎች መካናቸውን ለማረጋገጥ ከአንድ አመት ቅድመ ስልጠና በውኋላ በስራ ላይ የሁለት አመት ስልጠናና ሌሎችም ማሻሻያ ኮርሶችን እንዲወስዱ ያደርጋል።

## ምክር

አስተማሪዎቻችን እያንዳንዱን ተማሪ በኮርሱ ወቅት ያማክራሉ። ከኮርሱ ውጭም በሳምንት ለተወሰኑ ሳዓታት በነፃ የምክር አገልግሎት እንሰጣለን። ጀርመን አገር ጠቅልለው ለሚሄዱ የጀርመንን ባሕል ማስተዋውቂያ ክፍሎች በነፃ እንሰጣለን።

## ነፃ የትምህርት እድል

በየአመቱ ለሁለት ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች ሙሉ ወጪአቸው ተሽፍኖ ላንድ ወር ጀርመን አገር ቋንቋ እንዲማሩ ይደረጋል።

## እራስን ማስተማሪያ ቦታ በቤተ መጻህፍት ውስጥ

በቤተ መጻህፍት ውስጥ ያለው እራስን ማስተማሪያ ቦታ ጊዜውን በጠበቁ ማቴሪ ያልና ላፕቶፖች የተዘጋጀ ሲሆን እንዲሁም የጀርመንኛ ቃላት እና ሰዋሰው መለማመጃ ፣የድምጽ CD ፣ስለ ጀርመን ባህል የሚያትቱ ጽሁፎች ከዚህ በተጨማሪ በኮምፒውተር የታገዘ የቋንቋ መለማመጃ እና ሌሎችም ይገኛሉ።

## ነፃ የቤተ መጻህፍት አባልነት

መጻህፍት ቤታችን ለቋንቋ ተማሪዎች ምንም አይነት የአባልነት ክፍያ ሳይጠበቅ ባቸው መጻህፍት ቤቱን መጠቀም እንዲሁም መጻህፍትንና ፊልሞችን መዋስ ይችላሉ።



## የባህል ፕሮግራሞች

የጀርመንኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሊሳተፉባቸው የሚችሉ የፊልም ምሽቶች፣ ኮንሰርቶች፣ አውደ - ርዕዮች፣ ውይይቶች ይዘጋጃሉ። በዚህም የባህል ዕውቀታቸውን ያሰፋሉ።

በተለይ የገና በዓል፣ ወርሀዊ የፊልም ፕሮግራምና ውድድሮች ለቋንቋ ተማሪዎች ተብለው በየጊዜው የሚዘጋጁ ናቸው።

## ካፌ

ካፌ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና የዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች እንዲሁም የጎተ ሰራተኞችና ተማሪዎች መገናኛ ካፌ ሲሆን ጣፋጭ ምግቦችን ያዘጋጃሉ።

# ጎተ ኢኒስቲቱት ኢትዮጵያ

ከስድስት ኪሎ በዋናው ዩንቨርሲቲ በራፍ ወደ እንጦጦ ሲሄዱ ከሁለት መቶ ሜትር በኋላ በቀኝ በኩል የጎተ ኢንስቲቱት ጽሑፍ ያገኛሉ። በዚያ በቀጥታ ወደ ውስጥ መግባት ነው።

## የስራ ሰዓትና አድራሻ

የቋንቋ ኮርስ ቢሮ የስራ ሰዓት


| | |
|---|---|
| **ሰኞ፣ ማክሰኞ ፣ሐሙስና ዓርብ** | **ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት** |
| | **ከሰዓት በኋላ ከ 8 ሰዓት እስከ 11 ሰዓት 30** |

ቤተ መጽሐፍቱ ክፍት የሆነባቸው ቀናት

| | |
|---|---|
| **ሰኞ፣ማክሰኞ፣ሐሙስ፣ ዓርብ** | **ከ2 ሰዓት 30 እስከ 11 ሰዓት 30** |
| **ረቡዕ** | **ከ7 ሰዓት እስከ 11 ሰዓት 30** |

**በኢትዮጵያ ህጋዊ የበዓል ቀናት የቋንቋ ኮርስ ቢሮና ቤተ መጽሐፍቱ ዝግ ናቸው።**

**GOETHE-INSTITUT ADDIS ABEBA**








**Publisher**
2025, Goethe-Institut Äthiopien

**Design**
d-signbureau

**Printing**
Kriechbaumer GmbH & Co. KG

**Photo credits**
pages 1, 2 & 6 Barcot Wolde
Page 13 Bemnet Fekadu

አድራሻ
**Goethe-Institut Ethiopia**
Sedist Kilo,
College of Business and Economics
P.O. Box 1193
Addis Abeba, Ethiopia
Tel. + 251 11 1 24 23 45 / 46
E-Mail: ADD-lso@goethe.de
info@addis.goethe.de

**www.goethe.de/addisabeba**

**Goethe-Institut Ethiopia**
Sedist Kilo, Compound of College
of Business and Economics
Addis Abeba, Äthiopien
Tel. + 251 11 124 23 45/46
info-addis@goethe.de

**www.goethe.de/addisabeba**